# <u>የማይመስል ፀሎት -- አህያን ወደ ጠበል</u>

*ሀማ ቱማ*

በሀገራችን ብልሆች ሲተርቱ የባለጌ ሃይማኖት ከጅማት ይጠነክራል ብለዋል፡፡ ብዙ ሲጠብቅና ሲሳብ መበጠስ፤ ብዙ ሲከር ደግሞ ማነታረኩና ማናኮሩ የሚጠበቅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርሱ በርሱ በሰላም ለመኖር የቻለበት ጊዜ ሁሉ የግል ሀይማኖቱን ሳያከር ይዞ አንዱ ሌላውን ባከበረበት ጊዜ ነው፡፡ በሀይማኖት መጋጨት አገር አጥፊ ቅንጦት መሆኑን በማወቁም እንደ ቄስ ልጅ ተንጻላቆና ተጋድሞ ሊቆርብ ሳይከጅለው ባጅቷል፡፡

በፊት በፊት ያኔ፤ በድንጋይ ዳቦ ዘመን፤ በግ ቆዳ ምላሽ በአንድ ብር ሲሸጥ፤ ዘር ቆጠራን ብዙሃኑ ከቁጥር በማያስገባበት ዘመን ለማለት ዛሬ እያስከጀለን ነው ብንል ስህተት አይሆንም፡፡ ዛሬ ሁሉም በየፊናው የባለጌ ሀይማኖት በተባለው መንፈስ የየራሱን እያከረረ ለሌላው ትዕግስቱም፤ ከበሬታም ስለጠፋበት ሊጋደል ደፋ ቀና እያለ ነው፡፡ የሀገር ህልውና ለአደጋ በዚህ መንገድ ሲጋለጥ ደግሞ የጨው ተራራ ሲናድ ከት ብሎ እንደሚስቀው ሞኝ የሆኑ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ሀገር አጥፊው ወያኔ ሕዝብን በብሄረሰብም በጎጥም፤ በሀይማኖትም ለመከፋፈል በተቻለው እየጣረ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሌሎችም ለዚሁ ወፍጮ ባቄላ እያቀረቡ መሆናቸው፤ እሳቱን እያራገቡ መሆናቸው ደግሞ ግልፅ ነው፡፡ የሳውዲና ሌሎች አክራሪዎች ዋሀቢዝምና ሳላፊዝምን ማስራጨታቸው ሲታይ፤ ፀረ እስላም የሆኑና ሽብርተኛነትን መዋጋት በሚል ደግሞ ዘመናዊ ሚስዮናውያን በበኩላቸው ጎጂ ስራቸውን እየሰሩ ናቸው፡፡ በመሀል አብሮ የኖረው ሕዝብ በዚህና በዚያ እየተጎተተና ለአስከፊ ዕልቂትም እየታጨ--እየተዘጋጀ ነው፡፡ ይህ ሀቅ ሆኖ ሳል ተማርን አወቅን የሚሉ ግን ሀላፊነት የጎደላቸው በባዕድ ሀገር ያሉ የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ደግሞ የሀይማኖትን ግጭት ለማራገብ ሲባልጉ ማዳመጥና ማንበብ ተገደናል፡፡ ደግነቱ እስካሁን እነዚህ ፅንፈኞችና አናካሾች በጣም በጣም ጥቂት መሆናቸው ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሀይማኖት የወንጀለኛ መደበቂያ መሆኑንም እያየን ነው፡፡ በዘልማድ የበደለና ወንጀል የሰራ፤ያጠፋ፤ ገዳም ሄዶ መዝጋቱ የሚታወቅ ነው፡፡ የገዳም ኑሮ የሚኒሶታ፤ቶሮንቶና አውሮጳ ኑሮ አለመሆኑ ደግሞ ድብቅ አይደለም፡፡ ዋልድባ ሰው ሳያይ የተዘጋው በቋሪፍ መኖሩ ከቁርጥና ክትፎ በላተኛው፤ ከኮኛክ ውስኪ ጨላጬ ጋር አንድ ነው ካልተባለ በስተቀር ኑሮው ሰውነቱን እየበደለና እየቀጣ ነው፡፡ የንስሐ ሂደት ነው፡፡ፆም ፀሎት ነው፡፡ ቁንጫና ቅማል፤ትኋንን ፤ረሀብን መቻል፤ስሜትን ማፈን ነው፡፡ ዓመታት እንደ ጥላ አያልፉላቸውም፡፡ የዘንድሮዎቹ ወንጀለኞች ደግሞ የተለዩ ናቸው፡፡ በቆፈሩት ጉድጓድ አልገቡም፤ አልመነኑም፥ገዳም አልገቡም፡፡ በሀገር ከቆዩ እንደነተስፋዬ ቼንቶ ዘር ቆጥረውና ለአዲስ ባለስልጣን አድረው ማንም ሳይነካቸው ይኖራሉ፡፡ ከተሰደዱ ደግሞ እንደነ ዘገየ ሎሊሶ ጳንጤ ሆነናል፤ክርስቶስን ተቀብለናል ብለው ስለ ወንጀላቸው ፀፀት ሳያሰሙ (ዘገየ ወደ ኦሞ ወንዝ እጃቸው የታሰረ ኢሕአፓዎችን ከቶ በአዞ ያስበላ፤ ሊወጡ የጣሩትንም በክላሺን የረሸናነ ያስረሸነ አረመኔ ነው) አሁንም ተመችቷቸው ይኖራሉ፡፡ የብዙ ንፁህንን ደም ያፈሰሱ አረመኔዎች ከሀራሬ እስከ አምስተርዳም፤አታዋ ቶሮንቶ፤ ሚኒሶታ

ናይሮቢ ተሰራጭተው ዛሬም የትላንቱ ዛራቸው እያስጎራቸው ሲጮኹ እየሰማን ነው።ከትላንት ወደ ዛሬ ስንመጣ ደግሞ በሀገራችንና በሕዝባችን ላይ የማይናቅ ወንጀል የፈፀመው ታምራት ላይኔም ዓይኑን በጨው አጥቦ በከርቸሌ ክርስቶስን አገኘሁት ላልቅስ እሪ ልበል ተዉኝ ብሎ ካስደነቀን በኋላ የሰረቀውን ሚሊዮኖች ለወያኔ አስረክቦ ወደ ዴንቨር አሜሪካ ተጉዟል። ከሰለባዎቹ መሀል እነ ፀጋዬና ጓዶቹ የት እንደደረሱ እንኳን ሊናገር አልዳዳውም። ያሳዘነውና ያበሳጨው ጉዳይም የወያኔና ሻዕቢያ መጣላት መሆኑን ግን ነግሮናል። ታምራት ተቀበለችኝ ያላት ቤተ ክርስቲያን ራሷን ፀፀት ላላሰሙ ወንጀለኞች መደበቂያ ማድረጓ የሚያስጠይቃት ነው። ኢየሱስ ባርናባስን ማረው ሲባል የንስሐ ጥያቄ ቀድሞ እንደነበር አማኝ ነን ባሉት የተረሳ ይመስላል። (የንፁህ ሰውን ሕይወት ማጥፋት ማስጠፋት፣የሀገርን ህልውና መጉዳትን የሚያህል ወንጀል ለመሆኑ አለ?)

ሀይማኖትና ፖለቲካ ለየቅል ናቸው። ከቆጵሮሱ አቡን ፕሬዚዳንት እስከ ኢራን አያቶላዎች የታየው የተዛባና የተሳሳተ ነው።ሀይማኖት የግል ሀገር የጋራ ናትና የሀይማኖት መሪዎች በፖለቲካ ጣልቃ ሲገቡና ከስነ ስርዓት አልፎ ምድራዊ ህግ በአንድ ሀይማኖት ህግ መሰረት ይቃኝ ሲባል መዘዙ ቀላል አይለደም። የግለሰብ ነፃነትን ከመፃረሩ ባሻገር ሕዝብን ያጋድላል። ሩቅ ሳንሄድ የሱዳን ረጅም የደቡብ ጦርነት ይህንኑ አሳይቷል። የዴሞክራሲ መስፈን ገፅታው ብዙውን ጊዜ ሪፑብሊካዊ (ወይም ፈላጭ ቆራጭ ንጉስ የሌለበት) ነው ሲባል ከዚሁ ተያይዞ ደግሞ ሀይማኖትና ፖለቲካ መለየታቸውና በህብረተሰቡ ይህ መረጋገጡ (ሴኩላሪዝም መስፈኑ) ደግሞ ወሳኝ ነው። የወያኔ አገዛዝ የሀይማኖት ተቋሞችን ሊያፈርስ ወይም አንዱንና ሌላውን ሊያዳክም ሻጥር ሊፈፅም ሲቅነዘንዝ ብዙ ጉዳትን አስከትሏል።አደባባይ ኢየሱስና አንዋር መስጊድ፣ የአሰቦት ፍጅት ወዘተ ምሳሌ ናቸው። ለባዕዳንም በሩን ከፍቶ ሕዝባችንን አስጠቅቷል። በድህነታችንና ችግራችን ላይ ተመስርተው እምነታችን ላይ ሊቀልዱና የልባቸውን ሊፈፅሙ ይችሉ ዘንድ ሁኔታውን አመቻችቶላቸዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃም የሀይማኖት አክራሪ ንቅናቄዎች በዝተዋልናም ችግሩ ቀላል አልሆነም፣አይደለምም። ለዚህም ነው አክራሪና ከፋፋዮችን፣ ፅንፈኞችን መቋቋም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ የሚሆነው። ሀገር ተረስታ የእኔ ሀይማኖት ከሁሉም በላይ ማለት ከቀደመ ወደ ማያባራ ጦርነት መግባት አይቀሬ ይሆናል። ሀገርን በአንድ ሀይማኖት ደረጃ መግለፅም ከተገፋበት መዘዙ እንዲሁ ሆጂ ይሆናል።

ከዚህ ቀደም ይቅርታ እንጠየቅ በሚል ርዕስ ያቀረብኩት ፅሁፍ ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅ ሲገባቸው ያልጠየቁ ነፍሰ ገዳዮች፣ ዓይን አውጣዎችንና ክህደት--አደሮችን ቢያስቀይምም መሰረተ ሀሳቡ ዛሬ እየደረሰ ካለው ማጭብርበር ጋር የተያያዘ ነው። በሀይማኖታችን መሰረት ይቅርታ አድራጊ ክርስቶስ ወይ አላህ ነው በሚልና ማንም ባላወቀው ደግሞ ፈጣሪያችንን ተቀብለናል በሚል (በበኩሌ ይህ ክርስቶስን ተቀበልኩ የሚሉበት በለቅሶ የታጀበ ሂደት በናይሮቢ ጂቫንጂ መናፈሻ አየው ከነበረው አንድ ይሁን አይሁን ዝርዝሩን ባላውቀወም)-- ንስሐ መግባትንና ሕዝብን ይቅርታ መጠየቅን በዝምታ ያልፉታል። ለመሆኑ እነሱ ቢቀበሉትስ ክርስቶስ ሆነ አላህ እነዚህ

ንስሐ ያልገቡ ወንጀለኞችን ለመቀበሉ ምን ማስረጃ ያቀርባሉ? ይህን በዚሁ ትተን ወደ ተነሳንበት ስንመለስ የተበደለን ሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ በምንም ሰበብ የተነሳ ሊታለፍ ሊተው የሚችል አይደለም። ገለውና ፊጅተው ሲያበቁ አባ በሉን ወይም በቅተናል በፀሎት ሊሉ የሚቃጡትን ቧልታቸውን ማጋለጥ ያስፈልጋል። ለዚህ ነው ወያኔ ራሱ (እነ ስብሐተ ነጋ) በቀይ ሽብር ከተሳተፈ በኋላ የቀይ ሽብር ወንጀለኞችን ልፋረድ ስል የማያስቅ ቀልድ ነው ብለን ከጠዋቱ ያወገዝነው። ቆብ ያጠለቀ ሁሉ አባ፣ ቁራን የቀራና ዳዊት የደገመ ሁሉ ፃድቅ ነው ማለት አይቻልም። ዘመን ለፍስሐ ፣ዕድሜ ለንስሐ ነውና ሕዝብን የበደሉ ከሕዝብ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው። ድርጅቶችም ሀይማኖቶችም ለወንጀለኞች መደበቂያ ከሆኑ መጨረሻቸው ከቶም አያምርም። ስንቱ የቀይ ሽብር ወንጀለኛ በየድርጅቱ ተደብቆ ዛሬ አንቱ በሉኝ እያለ አይደል? ስንቱ የወያኔ መሪ ወንጀለኛስ ዛሬ አንድም የረባ ፀፀት ሳያሰማ ነፃ አውጪ ብላችሁ ስገዱልኝ ሊል ደፍሮ ይጮህ የለም? ዛሬም በአዲስ መልክ ዘረኛ ስርዓታቸውን ሊገፉብን ይራወጡ የለ? ስንቱስ ማፌሪያ ከሀዲ ሲያጨበጭብ አላየንም? ጅብ ከአህያ ይውል ዘንድ ከተፈቀደለት ጥፋተኛው ጅቡ አይደለም። በሕዝብ ትግል ላይ ዘግናኝ ወያኔያዊ ቀልድ ሲቀልዱ ቆይተው ዛሬ ከአለቃቸው በተጣሉ ብቻ--ያውም ስለ ወያኔ ወንጀል ምንም ሳይተነፍሱ-- ወዳጅ ብሎ ማቀፍ የሞኝ ልጅ ሁለቴ ይመታል የሚባለውን ያመጣብናል። አንዱ ከዚህ ቀደም ጦርነት እንሰራባችኋለን ብሎ የቧረቀብን የወያኔ መሪ የወንጀሉ ነገር ሲነሳ ይቅርታ ሊጠይቅ ቀርቶ፣ የወያኔን ጉድ ገበና ሊያጋልጥ ቀርቶ፣ በዕብሪት " ሂሳብ ላዋራርድ አልመጣሁም" ብሎ ዓይኑን በጨው አጥቦ ሲመፃደቅ ያጨበጨቡለት ከሀዲዎችና አንጃዎች መኖራቸውንም ታዝበናል።

ይህ ጠላትና ወዳጅን ያለመለየትና ለጠላት ለመጎንበስ ወኔን ሰልቦ የመኮልኮል የክህደት ልክፍት ዛሬ በተለይ ባዕድ ሀገር ያሉ አወቅን ባዮችን እያጠቃ ነው። በመሆኑም የሕዝብ ጎራ የተባለው ዘብረቅረቅ ብሎ መገኘቱ አልቀረም። የፖለቲካ የዕዳት መኪና ያለህ (!) ብለን የጮህነው ለዚህ ነበር። ይህን ያልተረዱ አንድም ቂም ነገሰ ሲሉን ሌሎች ደግሞ ሰዎቹ ስድብ ቀናቸው ብለው አማረሩብን። ለነገሩ የሀገራችንን ታሪክ ስንጎበኝ የባንዳና የከሀዲ ክስተት አዲስ አይደለም። "ቀሪን ገረመው፣ የአርበኞቹ ታሪክ" ብለው አቶ ታደሰ ዘወልዴ 40 ዓመት በፊት በፃፉት መፅሀፍ ከቀረበው ብንጠቅስ፣--

*" ኢትዮጵያ በጠላት ስትወረወርና ከጥንት ጀምሮ እስከጊዜያችን በጀግኖች ልጆቿ ተከላካይነት ተጠብቆ የኖረውን ነፃነት..የሚቀማ ወራሪ አገሪቷን እንደ አንበጣ መንጋ አልብሷት በታየበት ወቅት ሌላው አናስወስድም ብሎ በዱር በገደል ሆኖ ሲጋደል እኩለቴቹ ደግሞ ተጠብቆ የኖረውን ክብራቸውን አዋርደው ለጠላት በማጎንበስ ራሳቸውን ማስገዛት አንቧቸው ሞገስ እናገኛለን የማለት ተስፋ አድሮባቸው ሠርተው አዳሪዎችን በማስፈራራት ከርሻ ሥራቸው እያፈናቀሉና እየመለመሉ በነሱ በመታጀብና ከጠላት ጎን አሠልፈው ወንድሞቻቸውን እንዲገደሉ፣ የኢትዮጵያም ነፃነት ተደምስሶ ሕዝቦቿም በባርነት ሥር እንዲኖሩ ስለፈለጉት ሰዎች ምን እንላለን?*

*.......ያም ሆነ ይህ ሀገርን ክዶ በአርበኞች ጥይት ተመትቶ ከመሞት ስለ ሀገሩ ክብር ከጠላት ጋር  ሲከራከር ከሞተ ጀግና ሰው ክብሩ ለየትኛው እንደሚሆን ለይቶ ለማወቅ ከፍ ያለውን ፍልስፍና ይጠይቅ ኖሯልን? ....በ1928 ዓ.ም. የጦር ክተት ዓዋጅ የታወጀው ስለማይጨው ዘመቻ መሆኑ በግልፅ ቢታወቅም ጦርነቱ የቀጠለ ሆኖ ሲገኝ ውለታዬ ማይጨው ድረስ ነበር በዚያ በኩል የነበረው ከተፈፀመ አርበኞች በጠላት ላይ የሚያደርጉት ተቃውሞ እኔን አይመለከተኝም በማለት የገዛ ወገንን አዙሮ መውጋት ይኸን የመሰለ ወራዳ ተግባር ይዞ መገኘት በመልካ ም ታሪክ ዘንድ ቦታ የማይገኝለት ከመሆኑም በላይ የኢትዮጵያ ዜጋ ብሎ መጥራት እንኳን ቅር የሚያሰኝ ነው፡፡ በዚያን (በቀውጢ ጊዜ) አንዳንድ ሰዎች በጠላት ስብከት እየተታለሉ እንደ ተልባ ስፍር ሸርተት ሸርተት ሲሉ ማየታችን አሳዝኖናል፡፡ በዚያን ጊዜ ሞት የለም ነበር ለማለት ነው? ወራሪዊና ዋሾው ግራዚያኒ፤  ፊታውራሪ ፤ደጃዝማች፤ራስ፤ቢትወደድ፤ከባሊየሪ፤ ብያችኋለሁ የቀድሞውንም የባለነጋሪትነት መብታችሁን እመለስላችኋለሁ እያለ ቢወሽክትላቸው እንዴት ልብ ብለው አላመዛዘኑም?ታዲያ ኢትዮጵያ የፋሺስት ቅኝ አገር ከሆነች ማን ደሙን ባፈሰሰበት ሀገርበመንቀባረር  እንኖራለን የማለት ተስፋ እንዴት በልባቸው ውስጥ ሊቀረፅ ቻለ? የቀረው ቀርቶ  በዱር በገደል ሆነው ጠላትን የማጥፋት ዜዴ ችሎታ እያላቸው ላንድ ሁለት ዓመት ያህል እንኳን በመትረሰያቸው አፈሙዝ አንድና ሁለት ሳጥን ጥይቶች ሳያሸካኩበበት ለማስረከብ ባሰቡ ጊዜ ልባቸው ምን አለ? እነሱ እንኳን ለመንበርከክ ቢጣደፉም፤ፈቃደኞች ቢሆኑና መሳሪያቸውን ለሚሰሩ ቢሰጡት ምን ነበረበት? የክብር መለዮአቸውንስ ለማስረከብ እስከዚህ መጣደፍ ያስፈለገ በት ጉዳይ ምን ነበር? በቅድሚያ ምስጋና ለማግኘትና ለመሾም ነው?”*

የጠላትን ጦር አዛዥ አንድ ከሀዲ ተሸክሞ  ሥርጡን አወረደው ከተባለ በኋላም አርበኞች የሚከተለውን በሽለላ መልክ ነቅፈው ያቀረቡት ለዛሬም ይሰራል---

“ ጎበዝ ይሙት፤ ጎበዝ ይሙት፤ ፊሪ ይቁም ቢሻው
   አተላ መሸከም ይችላል ትከሻው፡፡”

ትከሻቸውን ለአተላና ለውርደት ያመቻቹ መበርከታቸው ለሀገራችን ቀውስን ፈጥሯል፡፡ ሀገር አድን ትግል ሆነ የቆረጠ የለውጥ ትግል በሕዝብ ና በሀገር ፍቅር ቢነሳሳም ጥላቻን ያዘለ መሆኑ ግድ ነው፡፡ በደፈናው ጥላቻን መስበኩ ባይገባም ሁሉን ውደዱ አፍቅሩ፤ ጠላትን እቀፉ የሚለው አጓጉል ሰበካ በፖለቲካው መስክ የውድቀት ክኒን ነው፡፡ ትግሉ ጠላቱ ላይ መነጣጠር አለበት፡፡ ታጋዩ ክፍልና ሕዝብ ደግሞ ጠላቱን በለዘብተኛ ደረጃ ሳይሆን በከረረ  ደረጃ መጥላቱ የግድ ነው፡፡ ድሮ ስለ አፄው ስርዓት ክፋትና መወገድ እንደሚገባውም ማለትም እንዲጠላ ለማድ ረግ ብዙ ቅስቀሳና ትግልን ጠይቋል፡፡ በዘመነ ደርግም ከኢሕአፓና ሌሎች ጥቂቶች በስተቀር ከአገዛዙ ሰምሮ የከረመው የአገዛዙን አረመኔነት ተረድቶ ለመጥላት ጊዜውን ውስዷል፡፡ ዛሬ ወያኔ ራሱ ወያኔን ይጠላል ለማለት በሚያስከጅል ደረጃ ላይ ነን--ሳር ቅጠሉ እነዚህን ወሮበሎችና

ፀረ ሕዝቦች አምርሮ ይጠላቸዋል። ይህ ደግሞ የሚያስደስተን ነው። በጠላቱ ላይ ያመረረ ጥላቻ ያለው ሕዝብ ድልን ሊቀዳጅ ይችላል። ይህ ጥላቻ እንዳይኖር የሚሰብኩን ሁሉ የሕዝብ ትግል ጠር የሚሆኑት በዚህ መልክ ነው። ህይማኖታዊ ጭምብል ያያዘ ዓይን አልባ ገደብ የለሽ ፍቅር መስባካቸው፣ ዘመን ተቀይሯል እንቻቻል ቅስቅሳቸው፣ ሰላማዊ ትግል በሚል ሽፋን መንበርከከን ማራመዳቸው፣ ወያኔን የሚጠሉትን በአክራሪነት መክሰሳቸው ወዘተ በዚህ የሚፈረጅ ነው። በአጭሩ፣ ወያኔን መጥላት ሲያንስ ነው። በመሆኑም የወያኔን ግብ ወደዱም ጠሉም የሚደግፉት ሁሉ የሕዝብ ተቃውሞና ጥላቻ  የሚዘንብባቸው መሆኑ ሊያስገርም አይገባም። በ1997ኡ ምርጫ የሕዝብን ትግል በተለይም የሙት ከተማ አድማን ከባዕዳን ተባብረው ያከሸፉትን ግለሰቦች ሕዝብ ቢጠላቸው ተገቢ ነው የምንለውም ለዚህ ነው። ከሰማዕት ደምና በየማጎሪያው ፍዳ ከሚቀ በሉት ወገኖች እንባና ሰቆቃ  ትምህርት መቅሰም ካልቻልን  እውነትም ስቃያቸውና መስዋዕትነ ታቸው በከንቱ ነበር ማለት እንገደዳለን። የቅርቡ የ 1997 መስዋዕትነት የሰጠንን ትምህርት ወግድ ብለን ዳግም ለወያኔ ተንኮል ሰለባ፣ ዳግም ለአስመሳይ ተቃዋሚዎች ሰለባ ከሆንን ተጠያቂ ራሳችን ብቻ ነን። ሽንኩርት አንዴም በሉት ገማ፣ደገሙትም ገማ ይባል የነበረውንም መርሳት የለብንም።

በመጪው ምርጫ መሳተፍ አለብን ብለው የተኮለኮሉት የለመዳበቸው ከሀዲዎች ዛሬ ደግሞ ተቃዋሚ ነበርን--ነን በሚሉ ያረጁ አዳዲሶች ታጅበዋል። ማንኛውም ድርጅት ባመነበት መንጎ ድ መብቱ ሆኖ ሳለ ጉዞው ደግሞ ከሕዝብ ጎራ ውጪ ከሆነ ከሽፈሀል--ተሳስተሃል ማለት ግዴታ ችን ነው። ጭፍን ጥላቻ ወይም  ድርጅቶች ላይ ዘመቻ ሳይሆን ሀገርን ከተምቾች መከላከል ነው ። መድረክ ተብለው የተሰበሰቡት የወያኔ ፓርላማ ተብዬ ወንበር አሟቂዎችና የቀድሞ ወያኔዎች ናቸው። እነዚህ የቀድሞ የወያኔ መሪዎች ዛሬም ልባቸው ወያኔ ከመሆኑ ሌላ ትላንት ለፈጁት ሕዝብ ደንታ የላቸውም። የወያኔን ቁንጮ ከቻሉ አስወግድው ካልቻሉም እሱንም ስርዓቱንም አጅበው የወያኔን የበላይነት አስፍነው መቀጠል ይመኛሉ። ይህን ምኞት የሚያጅቡ ከክልል አንድ ውጪ የሆኑ ከሀዲዎች ደግሞ መኖራቸው ሊያስገርም አይገባም። በተለይም ኢሕአፓ ነበር ን ብለው የሚለፍፉና ትላንት ጓዶች ያሏቸውን የጨረሱትን ጀግኖች ሲሉ ሰው ግራ ቢጋባ ቢደና ገር የሚፈረድበት አይሆንም። ክህደት ግን ራሱን የቻለ በሽታ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ሚቹ የወሊሶውን አባ ወልደተንሳይንም የማይሰማ ዛር ነው። ድርጅታቸውና ጓዶቻቸውን ነጋ ጠባ ሲከዱና ሲቆሽሹ የባጁ ማፈሪያዎች ድንገት ለውርደታቸው ለከት ሊያበጅሉት አይችሉም። ስጋ ነፍሳቸው ባይለያይም ሬሳነታቸውና ክርፋታቸው ግን የቆየ ነው። ስለዚህም የከሀዲን መንጋ ብንጠላ ሊፈረድብን አይችልም። በመሆኑም በዚህ በዚያ  ህብረት ስብስብ በሚል የሚደረገው ሩጫ መጨረሻው በመጀመሪያው የተበላሸ ክስተት ነው። ወንጀለኛ ወያኔዎች ተመልሰው የሕዝብ ነፃ አውጪ ሊሆኑ አይችሉም። በ1997 ሕዝብን የፈጀው አገዛዝ በ 2002 ዴሞክራት ሊሆን አይጠበቅም። የሕዝብን ትግል ያዳፈኑ ፈሪዎችና ከሀዲዎች ለጥፋታቸው መቸም ንስሐ ሳይገቡ ዛሬና ነገ ደፋር ቆራጥ የትግል መሪ ሊሆኑ መቸም አይሆንላቸውም። እነዚህን ሀቆች መገንዘብና መቀበል ግዴታችን ነው። ሀቅ የዘላለም ስንቅ ይባል የለ ? መልዕክቱን ባደረሰ መልዕክተኛውን

ለመግደል መራወጡም ከንቱ ነው።

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ ትውልድ የሚያስታውሰው ጀግናና ለሀገሩ ፀንቶ የቆመውን ነው። ጨቋኞችና ግፈኞች የበላይነትን እስከያዙ ድረስ በርግጥ ታሪክ ራሷ ለባለ ጉልበት እንድትሰግድ የብዕር ምንደኞች ክለሳን ሊያካሂዱ ይችላሉ። በዚህም የተነሳ ተሰፋ አስቆራጭ ሁኔታ፤ ዓለም ለባለጉልበት ሎሌ ናት የሚያሰኝ ሁኔታ ሊከሰት ይችላል።የፍትህ ሚዛን ያጋደለ መስሎ ሊታይ ም ይችላል፤ አንድ ህግና ሚዛን ለባለ ሀብት፤ ሌላ ህግና ሚዛን ለደሀው ለተጨቆነው። ሀቅን የበላይነት ማስያዙ የቃርሚያ ሩጫ ሊመስልም ይችላል። ግን ሀቅ ውላ አድራ በአናቷ ቢቀብሯት ም በእግሯ መውጣቷ አይቀርም። አንዳንዶች ታሪክ ሰሪው ሰፊው ሕዘብ ነው ሲባል ተናጋሪውን አብሸው ተነሳበት ለማለት ደቂቃም አይጠብቁም። ታሪክ ሰሪ ባለንፍጡ አገዛዝ፤ሀያል መንግስት የሚሉት፤ ተማረ አወቀ ምሁር ሆነ የተባለው ይመስሏቸዋል። ደብረ በጥብጡ የሰላም አባዋራ መስሎ ይገሸርባቸዋል። በንፁህ ዜጋ ደም የራሰው ካባ አይከረፋቸውም። ሜሮን ቅብዓ ቅዱስ የተቀባ ይመስላቸዋል። ታሪክ ሰሪ ግን ሰፊው ሕዝብ ፤ተራ ሕዝብ የሚባለው፤ እጁ የቀረፈደው፤ ፊቱ የጠቆረው የገረጣው ሕዝብ ነው።የአድዋ ድል ባለቤት አንድ ንጉስና ንግስት ሳይሆኑ ህይወ ቱን የገበረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ነውናም ውሎ አድሮ ጀግኖች በሕዝብ ተከብረዋል። ዛሬ አወቅን ባይ ግን በተጨባጭ መሀይሞች የታገሉትን ሲተቹ መስዋዕትነትን በማድነቅና በመዘከር ፈንታ ሕዝብን አስጨረሱ፤ ሕዝብ በባዶ አለቀ ብለው ሲያላዝኑ እንሰማለን። ሰሞኑን ያከበርነው የየካቲት 12 ሰማዕት ትምህርት ግን መልዕክቱ ሌላ ነው። አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስጌዶም በግራዚያኒ ላይ ቦምብ ወርውረው ሲያቆስሉት በበቀል እርምጃ ፋሺስቶች ብዙ ሺ ሰው ፈጅተዋ ል። ጀግኖቹን ሕዝብ አስፈጁ ያላቸው የለም። በጭልጋ ማህበረ ስላሴ አጠገብ ተይዘው በጣሊያ ን የተሰቀሉት ሁሉቱ አርበኞች በክብር አፅማቸው በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲ ያን አርፏል። ይህን በተመለከተ የቀሪን ገረመው መፅሀፍ ፀሀፊ በሚከተለው መልክ አስፍረውታ ል፤

*" የአብርሃ ደቦጭና የሞገስ አስገዶም የሕይወት ታሪክ ለወጣቱ ትውልድ ትልቅ ትምህርት ሊያስገኝለት ይቸላል። አንደኛ የሰው ልጅ የራሱን ክብርና ዝና ወይም ጥቅም ለማግኘት ከሚያ ደርገው ጥረት ይልቅ ለብሔራዊ ጥቅምና ዝና የሚደረግ መስዋዕትነት ሕያውነት ያለው መሆኑ፤ ሁለተኛ የሀገር ነፃነት ከተገፈፈ የማንም ሰው ነፃነት ሊከበር ስለማይችል ይህንኑ በመረዳት አብርሃ ደቦጭና ሞገስ አስጌዶም የፈፀሙት ተግባር ምንም እንኳን ድልን ባያስገኝ አድራጎቱ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ስሜት የሚያኮራና አርአያነቱ የሚጠቅም መሆኑ ነው።"*

ታሪክ ኃይለስላሴ ጉግሳን አውግዛ በላይ ዘለቀን ታደንቀዋለች። ባንዳና ፈሺሲቱን አውግዛ እነ ተስፋዬ ደበሳይን ትዘክራለች። መለስ ዜናዊን አብጠልጥላ ጋይምን ፀጋዬ ደብተራውን ጀግኖች ትላለች። በመሆኑም ዛሬ ለወያኔም ሆነ ለባዕድ ጡት አባቱ የሚሰግዱ ነገ ታሪክ ከትቢያ የምትከ

ታቸው መሆኑ መታወቅ አለበት:: ዛሬን ብቻ በማየትና ዕይታንም ወድ እንብርት በማተኮር የሚ ወሰድ ብልጣ ብልጥ አቅዋም ይነጋል ሌሊቱ ነውና ጎህ ሲቀድ ደብቁኝን ማስከተሉ አይቀርም:: ገመና ከታች ሰውም አያገኙም--ይጋለጣሉ:: ለዚህም ነው ከወዲሁ ሕዝብን ይቅርታ ጠይቁ፤ በሕዝብ ደም የረጠበ ልብሳችሁን ይዛችሁ ከሕዝብ ጎራ አትምጡ የምንለው:: ሰፊ ህብረትና መድረክ ብለው ተሰብስበናል ወይም ልንተቃቀፍ ነው የሚሉን በሞላ ጎደል ግም ለግም አብረህ አዝግም ለመሆናቸው መረጃ ጠያቂ አይኖርም:: የቀድሞ የወያኔ መሪዎች በሕዝብ ላየ ወንጀል የፈፀሙና አሁንም በዘረኝነት የባሰ ወንጀል ሊፈዕሙ የቋመጡ ናቸው:: አጃቢዎቻቸው ደግሞ የለየላቸው ከሀዲዎች ናቸው:: በባዕድ ሀገር ደግሞ በዚሁ የእርያ ጭቃ ገብተው ሊፈረጋጡ የሚሰ በሰቡትም ቢሆኑሀገር የምታፍርባቸው ጉዶች ናቸው:: በአጭሩ የመለሰ ዜናዊ የምርጫ አጃቢዎች አህያን ወደ ጠበል ሊወስዱ የተነሱ ጉዶች ናቸው::

ይህን ባልንና ባሳሰብን ደግሞ ውርጅብኙ መረን ለቆ መዝነቡ የማይቀር ነው:: ወያኔና ጭፍሮቹ፤ ሕዝብን የካዱት አንጃዎችና የታሪሻክ አተላዎች ሁሉ ሑሑ ማለታቸው የሚጠበቅ ነው:: መጋለጣ ቸው ይቆጠቁጣቸዋል:: ሕዝብ ግን ከወደቀበት ማጥ ወጥቶ ልብሱንም ራሱንም አጥቦ ጉዞውን ሊቀጥል ሲነሳ ዳግም ከማጥ ሊከቱት የሚያሴሩትን መከተል ሳይሆን አምርሮ መታገል አለበትና በተለይ አስመሳዮቹን ማጋለጥ ግዴታችን ነው:: ሂሳብ ለማወራረድ ጊዜ የለንም ለሚሉን ዕብሪተ ኞችና ጭፍሮቻቸው ደግሞ ሂሳብ ሳታወራርዱ ወዴት ጠጋ ጠጋ እንላቸዋለን፤ ልንላቸው ይገባል:: ክርስቶስን ተቀበልን ብለው እንባ ቢረጩም ሆነ መለስን ጠምደነዋል ብለው በደፈናው ቢመፃደቁም የምንታለልላቸው ልንሆን አይገባም:: መለስንም ከነአገዛዙ፤ እነርሱም ጭምር በነበሩ በት ጊዜም መጥምድ ብቻ ሳይሆን ጠልተናቸው አልነበር? በጋራ የሰጡን ቁስል ዛሬም ይቆጠቁ ጠን አይደል? ክህደታቸው እያስመረረን አይደል? የሳጥናዔል ጭፍሮች ከአለቃቸው ቢጣሉ ቀንዳቸውና ጭራቸው ይተናል?
ለታምራትና ጭፍሮቹም ቅዱስ ባለጌ ሲባል በመሰረቱ ልዩ ባለጌ እንጂ ቅዱስ ማለት አለመሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል::